# 50

# መሠረታዊ የተውሂድ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

## 2

ሐላል ሊሚትድ

COOPERATIVE OFFICE FOR CALL
AND GUIDANCE EASTERN JEDDAH
P.O. BOX : 102137 - JADDAH 21321 K.S.A.
TEL.: 6200005 (5 LINES) - FAX: 6240398

# 50

# መሠረታዊ የተውሂድ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

ሒላል ሊሚትድ
ስ.ቁ. 75 12 79/79 25 83
ፖ.ሣ.ቁ. 160239
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

بسم الله الرحمن الرحيم

# መግቢያ

«ተውሒድ» የኢስላማዊው ዕምነት መሠረታዊ ክፍል ሲሆን፥ በአላህና በሰዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግልፅና ጉልህ ያደርጋል።

እኛ ሙስሊሞች በአላህ አንድነት፣ ተንከባካቢነትና የፍጥረተ-ዓለሙ የበላይ ገዥነት እናምናለን። መመለክ የሚገባው ኃይል እርሱ ብቻ መሆኑን ከልብ እንቀበላለን።

የዚህች እጥር ምጥን ብላ የተዘጋጀች መጽሐፍ ዓለማ መሠረታዊ የተውሒድ ፅንሰ-ሐሳቦችን ማስጨበጥ ሆኖ፥ በጥያቄና መልስ መልክ ነው የተዘጋጀችው። 50 ያህል ጥያቄዎችንና መልሶቻቸውን አካታለች። የሚቀርቡት ጥያቄዎች እጅግ መሠረታዊና መልሶቹም አጭር፥ ግን አጥጋቢ እንዲሆኑ የሚቻለው ሁሉ ተደርጓል። መጽሐፏ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሰዎች ጠቀሜታ እንደሚኖራት ይታመናል።

አንባቢያን መጽሐፏ የያዘቻቸውን ቁምነገሮች ክብደት በመገንዘብ በጥንቃቄ እንዲያነቧትና እንዲያጠኗት ግብዣ ቀርቦላቸዋል።

ሒ ላ ል ሊ ሚ ት ድ

**ጥያቄ-** *ጌታህ[1] ማን ነው?*

<u>መልስ:-</u> ጌታዬ እኔንና ሌሎችንም ፍጡራን የፈጠረ፣ እንዲሁም ፍጥረታትን በፀጋው የሚንከባከበው አላህ ነው።

**ጥያቄ-** *ሃይማኖትህ ምንድን ነው?*

<u>መልስ:-</u> ሃይማኖቴ ኢስላም ነው፤ በፍቅር፣ በተስፋና በፍርሃት ለአላህና ለመልዕክተኛው ትዕዛዞች ተገዥና ታዛዥ መሆን።

**ጥያቄ-** *አላህን እንዴት ልታውቅ ቻልክ?*

<u>መልስ:-</u> አላህን ላውቅ የቻልኩት ፍጥረተ-ዓለሙን በመርመር ነው። ማለትም ቀንና ማታን፣ ፀሐይንና ጨረቃን፣ ሰማይና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ ፍጡራንን ሁሉ በማስተዋል።

**ጥያቄ-** *አላህ የት ነው?*

<u>መልስ:-</u> አላህ ከፍጥረታቱ ተለይቶ ከሰማየ ሰማያት በላይ ከዐርሹ ላይ ነው።

**ጥያቄ-** *አላህ ከእኛ ጋር ነው?*

<u>መልስ:-</u> አላህ ከተላቀው ዐርሹ ላይ ነው። ግና በዕውቀቱ፣ በመስማት፣ በማየትና በሌሎች ባህሪያት ከእኛ ጋር ነው። አላህ እንዲህ ይላል:-

---

[1] «ረብ» የሚለው የዐረብኛ ቃል አያሌ ትርጉሞች አሉት። ከነኝህም መሀከል የበላይ፣ ተንከባካቢ፣... የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው።

«(አላህም) አለ፡- አትፍሩ፤ እኔ በእርግጥ ከናንተ ጋር ነኝና፤ እሰማለሁ፤ አያለሁም፡፡» (20 ፥ 46)

**ጥያቄ**- *የአላህ ወዳጆች እነማን ናቸው?*

**መልስ፡-** የአላህ ወዳጆች ጥንቁቆችና መልካም መሪዎች ናቸው፤ አላህን በእጅጉ የሚፈሩ፥ ከኃጢአት የራቁ፥ ከወንጀል የተጠበቁ፥ መልካም ሥራዎችን ለሚፈጸም የሚጥሩ፥ ቁርአንና ሱንናን አጥብቀው የያዙ የአላህ አገልጋዮች፡፡

**ጥያቄ**- *አላህን የምትገዛው በምን አኳኋን ነው?*

**መልስ፡-** አላህን የምገዛው የማደርገው ዒባዳህ ሙሉ በሙሉ ለእሱ ብቻ በሚሆን አኳኋን ነው፡፡ በዒባዳዬ ከእርሱ ውጭ ማንንም ምንንም በእርሱ ላይ ሳላጋራ፡፡

**ጥያቄ**- *አላህ መልዕክተኞችን የላካቸው ለምንድን ነው?*

**መልስ**፡- አላህ መልዕክተኞችን የላከው ሰዎች አላህን ብቻ እንዲያመልኩና በእሱ ላይም ምንንም እንዳያጋሩ ጥሪ እንዲያደርጉ ነው፡፡ እንዲሁም የሰው ልጆች በአላህ ላይ ምንም ዓይነት አቤቱታ እንዳይኖራቸው፡፡

**ጥያቄ**- *የኢስላም ትርጉም ምንድን ነው?*

**መልስ**፡- ኢስላም ለአላህ (ለትዕዛዞቹ፣ ለሕግጋቱና ደንቦቹ...) እጅ መስጠት ነው፡፡

**ጥያቄ**- *የኢስላም መሠረቶች ምን ምን ናቸው?*

**መልስ**፡- የኢስላም መሠረቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1- የዕምነት ቃል ምስክር (ቃለ-ተውሒድ)፣
«ከአላህ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም፣ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው።»፣
2- ሶላትን አስተካክሎ መስገድ፣
3- ዘካትን መክፈል፣
4- የረመዷንን ፆም መፆም፣
5- ሐጅ -(የተከበረውንና የተቀደሰውን የአላህን ቤት መጎብኘት)፤ ችሎታው ላለው።

**ጥያቄ**- *ኢማን ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- ኢማን ማለት የዕምነት ፅንሰ-ሐሳቦችን ከልብ መቀበል፣ በምላስ መመስከር እና በአካላት (መልካም ተግባራትን) ማከናወን ነው።

**ጥያቄ**- *ኢማን ሊጨምርና ሊቀንስ ይችላል?*

<u>መልስ</u>:- አዎ፤ ኢማን ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።

**ጥያቄ**- *ኢማን ይጨምራል፣ ይቀንሳል ስትል ምን ማለትህ ነው?*

<u>መልስ</u>:- ኢማን ለአላህ ተገዥ ስንሆንና መልካም ሥራ ስንሠራ የሚጨምር ሲሆን፣ ኃጢአትና ክፉ ሥራዎችን ስንፈጽም ደግሞ ይቀንሳል።

**ጥያቄ**- *የኢማን መሠረቶች ምን ምን ናቸው? ቁጥራቸውስ ስንት ነው?*

<u>መልስ</u>:- የኢማን መሠረቶች ስድስት ናቸው። እነሱም:-

1- በአላህ ማመን፣
2- በመላእክቶች ማመን፣
3- በመልዕክተኞች ማመን፣

4- በቅዱሳን መጻሕፍት ማመን፣
5- በትንሳኤ ቀን ማመን፣
6- ማንኛውም ነገር፥ በጉም ይሁን ክፉ፥ የሚፈፀመው በአላህ ፈቃድና ውሳኔ መሆኑን ማመን ናቸው::

**ጥያቄ**- *በአላህ ማመን ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- አላህ ብቸኛ ፈጣሪ፣ አስተዳዳሪ (ተቆጣጣሪ)፣ መጋቢና የሁሉም ጉዳይ አስተናባሪ መሆኑን ማመን ነው:: ሁሉም ነገር የእሱ ጥገኛ ሲሆን፥ እሱ ግን የማንም ጥገኛ አይደለም:: ዒባዳ የሚገባው ለእሱ ብቻ ነው:: መልካምና የተዋቡ ስሞች፥ እንዲሁም ፍፁም የሆኑ ባህርያት አሉት::

**ጥያቄ**- *የመላእክታንን ምንነትና መሰያ ባህሪ ጥቀስ::*

<u>መልስ</u>:- መላዕክታን ከብርሃን የተፈጠሩ የአላህ አገልጋይ ፍጡራን ናቸው:: አላህን አይወነጀሉም ያዘዛቸውን በትክክል ይከውናሉ::

**ጥያቄ**- *ከአላህ በተዋረዱ መጽሐፍትና በመልዕክተኞች ማመን ማለት ምን ማለት ነው?*

<u>መልስ</u>:- አላህ ኑሕን፣ ኢብራሂምን፣ ሙሳን፣ ዒሳንና ሌሎችንም አያሌ መልዕክተኞች ልኳል:: ተውራትን፣ ኢንጂልንና ሌሎችንም መለኮታዊ መጽሐፍት አውርዷል:: የነቢያት ተልዕኮ የሰው ልጆች አላህን ብቻ ያለምንም ማሻረክ እንዲያመልኩት ጥሪ ማድረግ ነው:: የነቢያት መቋጫ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው:: ለሌሎች ነቢያት የተላኩ መጻሕፍት በቁርአን ተሽረዋል:: ስለዚህ አላህ መመለክ የሚገባው ቁርአን ባስተማረውና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተግባር ባሳዩት መልኩ ሊሆን ይገባል::

**ጥያቄ**- *በመጭው ዓለም (አኼራ) መኖር አምናለሁ ማለት ምን ማለት ነው?*

<u>መልስ</u>:- በመጭው ዓለም መኖር ማመን ማለት አላህ በዚህች ዓለም ላይ ላለ እያንዳንዱ ነገር ቀነ-ቀጠሮ እንዳደረገለት መቀበል ነው:: ዓለም ትጠፋለች:: የሰው ልጆችና ሌሎች ፍጥረታትም በሙሉ ይሞታሉ:: አላህ ሰዎችን ከመቃብር እንዲቀሰቀሱ ያደርጋቸዋል:: እናም በዚህች ዓለም ውስጥ ለፈፀሙት ክፉም ይሁኑ በጎ ተግባራት ይጠይቃቸዋል:: ለሠሩት መልካም ሥራ ይከሳቸዋል:: በጥፋታቸው ደግሞ ይቀጣቸዋል::

**ጥያቄ**- *በቀደር ማመን ትርጉሙ ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- በቀደር ማመን ማለት በዚህች ዓለም ላይ እያንዳንዱ ክንውን በአላህ ዕቅድና ፕላን መሠረት መፈፀሙን ከልብ መቀበል ነው:: አላህ ሁሉንም ነገር የፈጠረው በዕቅድና ፕላን (ቀደር) ነው::

**ጥያቄ**- *«ከአላህ ሌላ አምላክ የለም» የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- ትክክለኛ እውነተኛ አምላክ አላህ ብቻ ነው፣ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ማለት ነው:: ከአላህ ውጭ ያሉትን አማልክት ሐሰተኛ መሆናቸውን መናዘዝና ብቸኛውና እውነተኛ አምላክ አላህ ብቻ መሆኑን ማዕደቅ ነው::

**ጥያቄ**- *«ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው» የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- እርሳቸው ያዘዙንን ነገሮች ሙሉ በሙሉ መቀበልና ከከለከሉን ነገሮች ሙሉ በሙሉ መከልከል፣ እንዲሁም

ያስተላለፉልንን መልዕክት ከልብ አምነን መቀበል ማለት ነው።

**ጥያቄ**- *የዕምነት ምስክርነት መግለጫዎች ምን ምን ናቸው? ቁጥራቸውስ?*

<u>መልስ</u>፦ የዕምነት ምስክርነት መግለጫዎች ሰባት ናቸው። እነሱም፦

1- ዕውቀት- የማይምነት ተቃራኒ።
2- «የቂን» (እርግጠኝነት)- የጥርጣሬ ተቃራኒ።
3- «ኢኽላስ» (ቅንነት)- የሽርክ ተቃራኒ፣ የ«ኒያ» ተአማኒነትና ንጹህነት።
4- እውነተኝነት- የአስመሳይነት ተቃራኒ።
5- ፍቅርና ፅናት- የአላህን ሃይማኖት የመተው ተቃራኒ።
6- ታዛዥነትና ተገዢነት- የአመጸኝነት ተቃራኒ።
7- በሙሉ ልብ መቀበል- የእምቢተኝነትና የክህደት ተቃራኒ።

**ጥያቄ**- *ለሳህ ያዘዘን ትልቁ ነገር ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>፦ አላህ ያዘዘን ትልቁ ነገር «ተውሒድ» -የአላህ አሃዳዊነት- ነው።

**ጥያቄ**- «ተውሒድ» ምንድን ነው?

<u>መልስ</u>፦ ተውሒድ ከአንድ አላህ ሌላ በትክክል ሊገዙት የሚገባ አምላክ አለመኖሩንና አላህ ራሱ ወይም መልዕክተኛው የርሱን ማንነት ለመግለጽ የተጠቀሙባቸውን የባህርያት ስሞች ማጽደቅ ነው።

**ጥያቄ**- *የተውሒድ ዘርፎች ምን ምን ናቸው?*

መልስ:- ሦስት የተውሒድ ዘርፎች አሉ:: እነሱም:-

1- «ተውሒድ አሩቡቢየህ» (የተግባር አሃዳዊነት)፣
2- «ተውሒድ አል-ኡሉሂያ» (የተመላኪነት አሃዳዊነት)፣
3- «ተውሒድ አል-አስማእ ወሲፋት» (የባህርያትና የተዋቡ ስሞች አሃዳዊነት) ናቸው::

**ጥያቄ**- *«ተውሒድ አሩቡቢየህ» (የተግባር አሃዳዊነት) ምንድን ነው?*

መልስ:- አላህ በሥራዎቹ -በመፍጠር በማስተናበር ሕይወትን በመለገስም ሆነ በመንፈግ ወዘተ- አንድና ብቸኛ መሆኑን ማምኖ መቀበል ነው::

**ጥያቄ**- *«ተውሒድ አል-ኡሉሁያ» (የተመላኪነት አሃዳዊነት) ምንድን ነው?*

መልስ:- እንደ ሶላት፣ ዘካት፣ ፆም፣ ሩኩዕ፣ ሱጁዳና መሠል የአምልኮ ክንውኖች[2] መፈፀም ያለባቸው ለአላህ ብቻ መሆኑን ማጽደቅ ነው::

**ጥያቄ**- *«ተውሒድ አል-አስማእ ወሲፋት» (የባህሪያት አሃዳዊነት) ምንድን ነው?*

መልስ:- የአላህን ስሞችና ባህርያት በቁርአንና ሱንና ውስጥ በተጠቀሱበት አኳኋን፣ ከልዕልናቸው ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዳሉ መቀበል ነው::

**ጥያቄ**- *ዒባዳን እንዴት ትገልጸዋለህ?*

---

[2] በኢስላም አምልኮ (ዒባዳ) በነኝህና መሰል የአምልኮ ክንውኖች ብቻ የሚገደብ አይደለም:: እያንዳንዱን የሕይወት ዘርፍ ይመለከታል::

**መልስ**:- ዲባዳ አላህ የሚወዳቸውንና የሚደሰትባቸውን -ተግባራትና ቃላት- የሚያካትት አጠቃላይ ቃል ነው።

**ጥያቄ**- *የዒባዳ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?*

1- ለአላህ ፍፁም ታማኝ ሆኖ መገኘት።
2- ለአላህ መልዕክተኛ ታዛዥ መሆንና ሱንናቸውን መከተል።

**ጥያቄ**- *ጥቂት የዒባዳ ዓይነቶችን ዘርዝር።*

**መልስ**:- ከዒባዳ ዓይነቶች ጥቂቶቹ:- ሶላት፣ የግዴታ ምፅዋት፣ ፆም፣ ሐጅ፣ አላህን መፍራት፣ እገዛውን ተስፋ ማድረግ፣ እርዳታውን መከጀል እና ያዘዛቸውና ግዴታ ያደረጋቸው ሌሎች የአምልኮ ክንውኖች ናቸው።

**ጥያቄ**- *አላህ ከምንም በላይ አጥብቆ የከለከለው ነገር ምንድን ነው?*

**መልስ**:- አላህ እጅግን የከለከለው ነገር ሺርክ (ከአላህ ጋር ሌላ አማልክትን ማጋራት) ነው።

**ጥያቄ**- *በአላህ ማጋራት (ሺርክ) ምንድን ነው?*

**መልስ**:- በተግባራቱ አላህ ሊጋራ የሚችል ሌላ አካል ይኖራል ብሎ ማመን፣ ማለትም ለአላህ ተጋሪ ማድረግ ወይም በአላህ መብቶች ላይ ተቀናቃኝ ማበጀት ነው።

**ጥያቄ**- *የሺርክ -የማጋራት- ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?*

**መልስ**:- የሺርክ ዓይነቶች ሦስት ናቸው። እነሱም:-

1- ትልቅ ሺርክ (ሺርኩል አክበር)፣

2- መለስተኛ ሺርክ (ሺርኩል አስገር)፣
3- ድብቅ ሺርክ (ሺርኩል ኸፍይ) ናቸው።

**ጥያቄ**- *ትልቅ ሺርክ (ሺርኩል አክበር) ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>፡- ትልቅ ሺርክ -ማንኛውንም ዓይነት ዒባዳ ከአላህ ውጭ ለሌላ ማድረግ ሲሆን፣ በዚህ ዓይነት ሺርክ ላይ ለሞተ ሰው አላህ ምህረት አያደርግለትም። መልካም ሥራዎቹንም አይቀበልም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከኢስላም ጐራ ውጭ ነው።

**ጥያቄ**- *የትልቁ ሺርክ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?*

<u>መልስ</u>፡- የትልቁ ሺርክ ዓይነቶች አራት ናቸው። እነሱም፡-

1- የልመና (ዱዓ) ሺርክ- ከአላህ ውጭ ሌላን ሃይል መለመን፣
2- የ«ኒያህ» ሺርክ- የአንድን ክንውን ዓላማ «ኒያ» ከአላህ ሳይሆን፣ ከሌሎች አማልክት ጋር ማቆራኘት፣
3- የታዛዥነት ሺርክ- የአላህን ትዕዛዝ በሚቃረን መልክ፣ ለማንኛውም አካል ታዛዥ መሆን፣
4- የፍቅር ሺርክ- ለአላህ ብቻ የሚገባውን ፍቅር ለሌሎች ማድረግ።

**ጥያቄ**- *መለስተኛ ሺርክ (ሺርኩል አስገር) ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>፡- መለስተኛ ሺርክ ሪያእ ሲሆን፣ ይህም የዒባዳ ክንውኖችን አላህን ለማስደሰት ሳይሆን ለሌላ ዓላማ መፈፀም ነው። የዚህ ዓይነቱ ሺርክ ፈጻሚውን ከኢስላም ጐራ ውጪ አያደርገውም።

**ጥያቄ**- *ድብቅ ሺርክ (ሺርኩል ኸፍይ) ምንድን ነው?*

**መልስ**:- ድብቅ ሺርክ አላህ እንዲከሰቱ በፈቀዳቸው ሁኔታዎችና ክስተቶች ከአለመርካት የሚመነጭ የሺርክ ዓይነት ነው::

**ጥያቄ**- *ድብቅ ሺርክ ስመኖሩ ከቁርአን ወይም ከሐዲስ ዋቢ ጥቀስ::*

**መልስ**:- ተከታዩ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለዚህ ዓይነቱ ሺርክ ማረጋገጫ (ዋቢ) ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:-

«ሺርክ በዚህ ኡማህ (ሕዝበ-ሙስሊም) ውስጥ፥ ጥቁር ጉንዳን በጥቁር ድንጋይ ላይ በጨለማ ምሽት በምታደርገው ጉዞ ከሚሰማው የኮቴ ድምጽ ይበልጥ የተደበቀ ነው::»

**ጥያቄ**- *የ«ኩፍር» (ክህደት) ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?*

**መልስ**:- የኩፍር ዓይነቶች ሁለት ናቸው:-

1- ከኢስላም ውጪ የሚያደርግ (ትልቁ) ኩፍር
2- ከኢስላም የማያስወጣ እና የአላህን ፀጋ እርሱ ለፈቀደው ግልጋሎት ካለማዋል የሚመነጭ መለስተኛ ወይም ትንሹ ኩፍር ናቸው::

**ጥያቄ**- *የትልቁ ኩፍር ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?*

**መልስ**:- የትልቁ ኩፍር ዓይነቶች አምስት ናቸው::

1- የክህደት ኩፍር፣
2- እውነትን በጥልቅ እየተረዱ ያለመቀበል (የእምቢተኝነት) ኩፍር፣
3- የጥርጣሬ ኩፍር፣

4- የአላህን መልዕክትና ትዕዛዝ ከማድመጥ የመሸ
   ሸግ ኩፍር፣
5- የሙናፊቅነት ኩፍር።

**ጥያቄ**- *የሙናፊቅነት ዘርፎች ምን ምን ናቸው?*

<u>መልስ</u>:- ሁለት የሙናፊቅነት ዘርፎች አሉ። እነሱም:-

1- የዕምነት ሙናፊቅነት።
2- የተግባር (የሥራ) ሙናፊቅነት።

**ጥያቄ**- *የዕምነት ሙናፊቅነት ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- ስድስት ዓይነት የዕምነት ሙናፊቅነቶች አሉ። እነሱም:-

1- መልክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) መካድ፣
2- መልክተኛው የተላኩበትን ነገር (በከፊል ይሁን በሙሉ) መካድ፣
3- መልክተኛውን መጥላት፣
4- መልክተኛው የተላኩበትን ነገር (በከፊል ይሁን በሙሉ) መጥላት፣
5- በኢስላም ውድቀት መደሰት፣
6- የኢስላምን መጠናከር መጥላት፣

**ጥያቄ**- *የተግባር (የድርጊት) ሙናፊቅነት ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>:- አምስት ዓይነት የተግባር (የድርጊት) መናፍቅነቶች አሉ። እነሱም:-

1- ሐሰት መናገር፣
2- ቃል ኪዳንን ማፍረስ፣
3- ሲታመኑ መክዳት፣

4- ሲከራከሩ መሞገድ፣
5- ሲዋዋሉ ማታለል::

**ጥያቄ**- *ከሺርክ ጋር መልካም ሥራስ አላህ ዘንድ ተቀባይነት አለውን?*

<u>መልስ</u>:- ከሺርክ ጋር የተቀላቀለ ማንኛውም መልካም ሥራ በአላህ ዘንድ ተቀባይነት የለውም::

﴿ وَلو أشرَكوا لحَبِطَ عنهُم مَاكَانوا يَعلَمون ﴾ سورة الأنعام

«ይህ የአላህ መምሪያ ነው:: በርሱ ከባሮቹ የሚሻውን ሰው ይመራል፣ ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር::» (6 ፥ 88)

إِنَّ اللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ
ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ۚ وَمَن يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَٰلًا بَعِيدًا

«አላህ በርሱ ማጋራትን አይምርም፤ ከዚህም ወዲያ ያለውን ለሚሻው ሰው ይምራል:: በአላህም የሚያጋራ ሰው፣ (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ::» (4 ፥ 116)

**ጥያቄ**- *ኢስላምን የሚያበላሹ ነገሮች ምን ምን ናቸው?*

<u>መልስ</u>:-ኢስላምን የሚያበላሹ ነገሮች አሥር ናቸው:: እነሱም:-

1- የዒባዳ ሺርክ፤
2- የሙሽሪኮችን ክህደት አለማዕደቅ፣ ተቀባይነት እንደ ሌላቸው መጠራጠር ወይንም የዕምነታቸውን ትክክለኛነት መቀበል፤
3- በአላህና በሰዎች መካከል የሚለመኑ፣ ሰዎች የሚመኩባቸውና አማላጅ (ሽፋዕ) ደላላዎችን ማድረግ፤

4- በሌሎች ሃይላት የተነደፉ መመሪያዎች መልዕክተኛው ይዘውት ከመጡት መለኮታዊ መመሪያ የተሻሉ ናቸው ብሎ ማመን፤
5- መልክተኛው የተላኩበትን ነገር (በሙሉም ይሁን በከፊል) መጥላት፤
6- መልክተኛው ይዘውት በመጡት ሃይማኖት ወይም በምንዳና ቅጣቱ መቀለድ፤
7- ድግምት፤
8- ለሙስሊሞች በጠላትነት ከተሰየሙ ሙሽሪኮች ጋር መወገን፤
9- ሰይድ ኸድር ሙሳ ይዘውት የመጡትን መለኮታዊ ድንጋጌ «መቃረን» የሚፈቀድላቸው እንደቻሉ ሁሉ ነቢዩ ሙሐመድ ያመጡትንም መለኮታዊ ድንጋጌ «መቃረን» የሚፈቀድላቸው ሰዎች ይኖራሉ ብሎ ማመን፤
10- ከአላህ «ዲን» መሸሽ፤ ይህን ለማወቅና ለመተግበር ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረግ።

**ጥያቄ**- *ማንኛውም ሙስሊም መማር ያለበት ሦስቱ መሠረታዊ ነገሮች ምንድን ናቸው?*

<u>መልስ</u>፡- ሦስቱ መሠረታዊ ነገሮች፡-

1- ፈጣሪውንና የበላይ ገዥውን አላህን ማወቅ፤
2- ዲኑን ማወቅ፤
3- መልክተኛውን ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ማወቅ።

**ጥያቄ**- *ጣኦት ምንድን ነው?*

<u>መልስ</u>፡- ከአላህ ሌላ ሰዎች የሚገዙት፣ የሚከተሉት ወይንም የሚታዘዙት ማንኛውም ሃይል ጣኦት ይባላል።

**ጥያቄ**- *ስንት የጣኦት ዓይነቶች አሉ?*

<u>መልስ</u>፡- የጣጉት ዓይነቶች ብዙ ናቸው። ነገር ግን ቀንደኞቹ እምስት ናቸው።

**ጥያቄ-** *ቀንደኞችን የጣጉታት መሪዎች ጥቀስ።*

<u>መልስ፡-</u>

1- ሰዎች የአላህ ሌላ ያሉ ሃይላትን እንዲያመልኩ ሌት ተቀን ጥሪ የሚያደርገው ሰይጣን፤
2- የአላህ ህግጋትና ድንጋጌዎች የሚቀይር ግፈኛ ዳኛ፤
3- አላህ ባወረደው ህግ የማይፈርድና አላህ በቀረጸው ሥርዓት የማያስተዳድር መሪ፤
4- የሩቅ ሚስጥር (ገይብ) አውቃለሁ የሚል፤
5- እንዲመለክ ፈቅዶና ወደ ሰዎች የሚያመልኩት ማንኛውም ሃይል።

مطابع الدار الهندسية/القاهرة
تليفون/فاكس : (٢٠٢) ٥٤٠٢٥٩٨

# ٥٠ سؤالاً وجواباً عن التوحيد

اللغة الأمهرية


المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات في شرق جدة
تحت إشراف وزارة الشئون الإسلامية والأوقاف والدعوة والإرشاد
هاتف: ٦٢٠٠٠٥ (٤ خطوط) - فاكس: ٦٢٤٠٢٩٨ - ص. ب: ١٠٢١٣٢ - جدة: ٢١٣٢١